دار زايد للثقافة الإسلامية
Zayed House For Islamic Culture

# የሥልጣኔ ብዛህነት

ፀሐፊ ፡ ሻይካ ናስር አል ካርቢ

zhic.uae @zhic_uae zhic_uae zhic
800 555 اتصل على JUST CALL
P.O Box: 16090, Al Ain, U.A.E
www.zhic.ae contact@abudhabi.ae

የሥልጣኔ ብዛህነት ከቅርብ ጊዜ ወዲህ መንግሥታት በማኅበረሰቡ ውስጥ የሥልጣኔን ኃይል ለማንቀሳቀስ በተጨባጭ መሬት ላይ ለማዋልና የተለያየና በዓይነቱ የበዛ የሆነ፤ ግና ሁሉም የሌላኛውን ሥልጣኔ የሚያከብር የሆነ ማኅበረሰብን ለመገንባት ሊጠቀሙባቸው ከሚፈልጓቸው ትላልቅ የጊዜው ጽንሰ ሀሳቦች መካከል አንዱ ነው፡፡

የሥልጣኔ ብዛህነት ፅንሰ-ሀሳቡ ለተለያዩ ዓይነት ሥልጣኔዎች፣ አመለካከቶችና የሰው ልጅ ተሞክሮዎች ዕውቅና መስጠትን የሚያመለክት ነው፡፡ ሁሉም የሰው ልጆች ያደጉበት እና የታነፁበት የራሣቸው የሆነ የተወሰነ ሥልጣኔ አላቸው፡፡ ከዚህ አንፃር ደግሞ ሁሉም እንዲጠበቅላቸው የሚፈልጉ የየራሣቸው የሆነ ልዩነት፣ ቅርፅ እና ተፅዕኖ ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም የሥልጣኔ ብዛህነት የቱን ያህል የግለሰቦች ተሞክሮ እና ልምድ ቢለያዩም የሁሉንም ማኅበረሰብ መልካም እሴት ይጠብቃል፡፡

የሥልጣኔ ብዛህነት ለመንግሥትም ሆነ ለማኅበረሰቡ ትልቅ የሀብት ምንጭ ነው፡፡ የተለያዩ ዓይነት አመለካከቶች መኖራቸው የተለየ ውጤትን ያስገኛል፡፡ ለሰው ልጅ ዕድገት እና ከፍታ አስፈላጊ የሆኑ ልማትና ብልጽግናን ያመጣል፡፡ ሥልጣኔ አንድ ሰው በስሜት፣ በአመለካከትና በመንፈሳዊነትን እንዲጠናከር ያደርገዋል፡፡ የሥልጣኔ ብዛህነት እያንዳንዱ የማኅበረሰብ አባል ሚናውን እንዲያጎለብት ዕድል ይሰጠዋል፡፡ እያንዳንዱ ሰው ከሌላው ጋር የሚኖረው መስተጋብር የተስተካከለ እንዲሆንና ራዕይ እንዲሰንቅም ያደርጋል፡፡ ይህ መሆኑ ደግሞ ገንቢ የሆኑ ባህሪዎችን ያጠናክራል፡፡በመከባበር፣ አንዱ ሌላኛውን በመቀበል እና በመተጋገዝ ላይ የተመሠረተ ሥልጣኔን ለማጽናትም ያግዛል::

የሥልጣኔ ብዛህነት በርካታ ፋይዳዎች አሉት፡፡ ከነኚህም መካከል በአንድ ጥላ ሥር የተለያዩ ሥልጣኔዎችን የያዘ አዲስ አመለካከት በመፍጠር በአንድ ማኅበረሰብ ውስጥ ያሉ አባላትን የፈጠራ መንፈስ ማበልፀግ ይቻላል፡፡ ይህም ፍሬያማ የሆነ ውይይት እና ፈጠራን ያረጋግጣል፡፡ ከዚህም ሌላ የኢኮኖሚ እና የንግድ ልውውጥ በማድረግ የምጣኔ ሀብት ብልፅግናን ያስገኛል፡፡ ይህ ደግሞ የሥልጣኔ ብዛህነትን አስፈላጊነት የግድ እንደሆነ የሚፀና ነው፡፡

ዓለም ወደ አንዲት መንደር ተቀይራለች ማለት እንችላለን፡፡ በተለይ የሥልጣኔ ብዛህነት ፅንሰ ሀሳቡ እየሰፋና ጥቅሙም እየጎላ ከመጣ ወዲህ፡፡ ዋና ጭብጡም በዘመናዊው ሥልጣኔ ውስጥ ሁሉም ሥልጣኔውን እና ማንነቱን እንዲያንፀባርቅ ዕውቅና መስጠት ነው፡፡ በዚህም የተነሳ የነርሱ መገኘት በኩራት፣ በደስታ እና በወንድማማችነት ወደ ዓለማቀፋዊነት ለመንደርደር መነሻ ይሆናል፡፡